ለፀረ-ዲሞክራሲ ኃይሎችና ካድሬዎቻቸዉ ግንዛቤ 10 ነጥቦች
ከዶ/ር በቀለ ገሠሠ (ግንቦት 2012 ዓ/ም)

<u>መንደርደሪያ፤</u>

ንፁሐን የኢትዮጵያ ልጆች በተለይ ባለፉት 50 ዓመታት ለመሬት ላራሹ፤ ለዲሞክራሲ፤ ለእኩልነት፤ ለሰላምና ለአገር ዕድገት በመታገል ዉድ ሕይወታቸዉን በመስዋዕትነት እንደገበሩ ታሪክ ሁልጊዜ ሲያስታዉሳቸዉ ይኖራል። የአምባገነን ስርዓት አንቀሳቃሾችና ካድሬዎቻቸዉ በጭፍን ይሰለፋሉ፤ ሃቆች ያዛባሉ፤ የዋሆችን ያታልላሉ፤ ለሆዳቸዉ ሲሉ እስከመግደል ይደርሳሉ። አገሪቱ ግን ከድህነት ልትላቀቅ አልቻለችም፤ ችግሮችዋ እየበዙ ሄዱ፤ ጎልዉናዋን ጭምር አደጋ ላይ ያደርሳሉ። እስቲ የሚከተሉትን ግንዛቤዎች እንካፈል፤ ስህተት ካለበት ልታረም።

<u>የግንዛቤ ነጥቦች፡</u>

1ኛ/ የኢትዮጵያ ወዳጆች ህዝቧና ፈጣሪዋ ብቻ ናቸዉ። ለዚህ ነዉ ሁል ጊዜ 'ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች'። 'ኢትዮጵያ ታበጽሕ ኢዴዊሃ ሃበ እግዚአብሔር' የተባለዉ ያለ ምክንያት አልነበረም፤

ሀ) በፀፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት በተለይ እንግሊዞችን ዐይተናል፤ የመሪያችንን ሕይወት በመቅደላ ላይ ገብረናል።
ለ) በፀፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በተለይ ደርቡሾችን ዐይተናል፤ በመተማ ላይ የመሪያችንን ሕይወት ገብረናል።
ሐ) በፀፄ ምንሊክ ዘመነ መንግሥት በተለይ ጣሊያኖችን ዐይተናል፤ በአድዋ ላይ ሞክሩን፤ ግን አሳፍረን መልሰናቸዋል።
መ) በፀፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በተለይ ጣሊያኖችን እንደገና ዐይተናል፤ በማይጨዉና በ5 ዓመቱ እልህ አስጨራሽ የነፃነት ትግል ዘመናት ብዙ ሕይወት ገብረናል፤ ንብረቶቻችን ተቃጥለዉብናል።
ሠ) በደርግ ዘመነ መንግሥት የሶቪዬት ህብረቶች በለገሷቸዉ ጥይቶች ንፁሐን ዜጎቻችን ረግፈዋል፤ ምዕራባዉያንና የዐረብ አገሮች ደግሞ ኢትዮጵያን ለመበተን ተገንጣዮን እስከአፍንጫቸዉ ድረስ አስታጥቀዋል።
ረ) በደርግ ዉድቀት ዋዜማ ላይ ምዕራቦች ሁሉ-አቀፍ የሽግግር መንግሽት እንዲቋቋም አልፈቀዱም። በኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት ህዝባችንን በጎሣ በመሸንሸን የርስ በርስ ግጭቶች ጋብዘዋል:: አቢያተ ክርስቲያናትና መስጊዶች ተቃጥለዋል፤ ሰዉ በገዛ አገሩ በነፃነት የመኖር፤ የመዘዋወርና የመነገድ መብቱን ሸርሽረዋል፤ ህዝብን አፈናቅለዋል:: ከ6000 ዓመታት በላይ ህዝባችን በነፃ የሰፈረባትን አገር በምን መንገድ ሊሸነሽኑ ፈለጉ? ማን ከማን ይገነጠላል? ድንበሮችስ እንዴት አድርገዉ ሊያበጁላቸዉ ነዉ? ወይንስ እርስ በርስ እየከፋፈሉን ሊያስጨርሱንና እግዚአብሔር ባርኮ የሰጠንን ምድር ሊወስዱብን ነዉ? በሰሜን አሜሪካ፤ በአዉስትራሊያ፤ በኒዉዚላንድ፤ ወዘተ ስለተሳካላቸዉ እኛንም ሊያጠፉን ይሆን? እንበርታ ጎበዝ፤ እንሞኝ፤ በአንድነትና በእግዚአብሔር ኃይል ዉድ አገራችንን እንጠብቃት።
2ኛ/ የሰዉ ልጅ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶቹ መጠበቅ ይኖርባቸዋል።
3ኛ/ የዲሞክራሲ ግንባታ መብቱ በጉልበት እየታፈነ መቀጠል የለበትም።
4ኛ/ ዲሞክራሲ ከሌለ የህዝባችን መሠረታዊ መብት አይጠበቅም።
5ኛ/ መብት ካልተጠበቀ ሰላም አይኖርም። ሰላም ከሌለ ዘላቂ ዕድገት ሊኖር አይችልም።
6ኛ/ ራሳችንን መቻል ስንችል ዕድሜ ልክ በልመናና በዉጪ ዕርዳታ መኖር ያሳፍራል።
7ኘ/ ይባስ ብሎ በልመና የተገኘ የዉጪ ዕርዳታ መመዝበር እጅግ አሳፋሪ ተግባር ነዉ።

8ኛ/ ህዝብ እየተራበ፤ እየተሰደደና የጎዳና ተዳዳሪ እየሆነ የአገር ንብረት በቢሊዮኖች እየሰረቁ ወደ ዉጪ ማሸሽ ከባድ ወንጀል ነዉ፤ ከባድ ኃጢያትም ነዉ። መመለስ አለበት።

9ኛ/ አሁን ያለዉ ሕገ መንግሥት የደርግ መንግሥት ሲወድቅ በገቡት የወያኔ/ኢህአዴግ ኃይሎች የተረቀቀ እንጂ ህዝቡን በትክክል ያሳተፈ አልነበረም። ስለዚህ ህዝቡ በጠየቀዉ መሠረት መሻሻል ይገባዋል። ይሄንን መብት ማንም ሊነፍግ አይችልም።
10ኛ/ ሁሉ አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግሥት መቋቋም ነበረበት፤ ህዝባችን ባለፉት 50 ዓመታት የታገለለትና የተነፈገዉ ጥያቄ ነዉ ። ሰላም መዉረድ አለበት። አንድነታችን መጠንከር አለበት። ዛሬ ማንንም ሳንጎዳ ወንዞቻችንን ገድበን ከጭለማና ከረሃብ እንዳንወጣ እንኳን የዉጪ ኃይሎች ከፍተኛ ማስፈራራትና ጫና እየፈጠሩብን ናቸዉ።

ባጭሩ ከ50 ዓመታት መራራ ትግሎችና ከፍተኛ መስዋዕትነቶች በኋላ ዛሬ ዉድ አገራችን በጣም በተሻለ የሰላምና ዕድገት ደረጃ ላይ መገኘት ነበረባት። መቼ ነዉ የምንማረዉ? በተለይ ሁል ጊዜ የማይታረሙ ግለሰቦችና ቡድኖች በደንብ እንዲያስቡበት ያስፈልጋል። አገር ከኪስ መቅደም አለበት። እግዚአብሔር ጥሩ ልቦና ይስጣቸዉ፤ ዉድ አገራችንን ይጠብቅልን።